King County



# የእድገት መዘግየት ላለባቸው ልጆች እና የአዕምሮ እና/ወይም የእድገት እክል ያለባቸው ሰዎች በ2024 የክልል ህግ አውጪ ቅድሚያዎች

የዕድገት መዘግየቶች እና የአእምሮ እና/ወይም የእድገት እክል (I/DD) ያላቸው አገልግሎቶች ዘላቂ እና ፍትሃዊነትን፣ አካታችነት እና የባለቤትነትን መንፈስ የሚፈጥሩ መሆን አለባቸው። የ2024 ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች፤ ያንን ራዕይ ለማሳካት እና በክልሉ በሙሉ ውስጥ ካሉ የተጎዱ ማህበረሰቦች የተገኙ ግብአቶችን ለማንፀባረቅ፣ የእድገት መዘግየቶች እና አካል ጉዳት ያለባቸው፣ እና ጥቁር፣ ነባር እና የቀለም ህዝቦች (BIPOC) ያማከለ መሆንን ነው።

www.kingcounty.gov/ddecsd

## ቅድሚያዎች

### ቅድሚያ 1

ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ቋንቋቸውን በሚናገሩ እና ለባህላዊ ፍላጎቶቻቸው ምላሽ በሚሰጡ ሰዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ያግዙ።

### ቅድሚያ 2

ለህፃናት እና ታዳጊ ህፃናት የቅድመ ድጋፍ (ESIT) ኤጀንሲዎች በመጀመሪያው ወር ለቤተሰቦች ለሚሰጡ አገልግሎቶች የልዩ ትምህርት ገንዘብ ድጋፍ ማግኘታቸውን በማረጋገጥ ያግዙ።

### ቅድሚያ 3

የሥራ ቅጥር እና የማህበረሰብ አካታች የሆኑ አገልግሎት አቅራቢዎች የሚከፈሉትን መጠንን በመጨመር፤ I/DD ያላቸው ሰዎች ሥራ እንዲያገኙ እና እንዲቀጥሉ፣ እና በማህበረሰቦቻቸው ውስጥ እንዲታቀፉ በማድረግ ያግዛል።

### ቅድሚያ 4

አቅምን ያገናዘበ መኖሪያ ቤት እና የመኖሪያ ቤት ድጋፎች I/DD ላለባቸው ሰዎች መኖራቸውን በማረጋገጥ ያግዙ።

### ቅድሚያ 5

I/DD ያላቸውን ሰዎች በብቃት ለማገልገል እንዲረዳ፣ ተጨማሪ በችሎታ የባህሪ ጤና አቅራቢዎችን ይቀጥራል፤ ያሰለጥናል።

2310_13388R_DevelopDisabLegisForum.ai

## ቅድሚያ 1 - የቋንቋ ተደራሽነት

ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ቋንቋቸውን በሚናገሩ እና ለባህላዊ ፍላጎቶቻቸው ምላሽ በሚሰጡ ሰዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ያግዙ።

ማንኛውም ሰው የፈለገውን ቋንቋ ቢናገርም እንኳ፣ አገልግሎት ማግኘት መቻሉንል ለማረጋገጥ በሁሉም ስርዓቶች እና ፕሮግራሞች ውስጥ የቋንቋ ተደራሽነት አስፈላጊ ነው። አገልግሎቶች ለቤተሰብ ባህልን ያገናዘቡ መሆናቸውም እንዲሁም አስፈላጊ ነው። ሰዎች እና ቤተሰቦች ባህላቸው፣ ታሪካቸው፣ እምነታቸው እና ቋንቋቸው ከእራሳቸው ጋር ተመሳሳይ ከሆኑ አቅራቢዎች ከሚቀበሉት አገልግሎቶች ይጠቀማሉ። ይንም ማለት የሚያገኙአቸው አገልግሎቶች አግባብነት ያላቸው፣ የሚዛመዱ፣ የሚደገፉ እና አድሎአዊነት የሌላቸው ናቸው ማለት ነው፡፡




የተለያዩ የአገልግሎት ሰነዶችን በእያንዳንዱ ግለሰብ እማ ቤተሰብ ተመራጭ ቋንቋ መተርጎም በጣም አስፈላጊ ነው፡ ነገር ግን ውድ ነው፡፡ ይህ ሁልጊዜም በኢንሹራንስ ለማይሸፈን ለተርጓሚዎችም ተመሳሳይ ነው፡፡ የህግ አውጭው፣ የእድገት እክል ጉዳተኞች አስተዳደር (DDA)፣ የህፃናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ፣ የሙያ ማገገሚያ ክፍል እና የጤና እንክብካቤ ባለስልጣንን ጨምሮ፣ ለክልል ኤጀንሲዎች የቋንቋ ተደራሽነት የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ፣ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የሚገባቸውን የአገልግሎት ጥራት ማበረታታት ይችላል፡፡



የአካል ጉዳት ያለባቸው ነዋሪዎችም ማለትም ጥቁሮች፣ ነባሪ ነዋሪዎች እና የቀለም ሰዎች ከዕድገት እክል፣ ጤና እንክብካቤ እና ከ**K-12** የትምህርት ስርአቶች ፍላጎታቸውን ለማሟላት መቸገራቸውን ለኪንግ ካውንቲ ተናግረዋል። ቤተሰቦች የዘር፣ የባህል እና የቋንቋ መድሎ እንዳጋጠማቸው ሪፖርት አድረገዋል፡፡


# ቅድሚያ 2

## ለህፃናት እና ታዳጊ ህፃናት የቅድመ ድጋፍ (ESIT) ኤጀንሲዎች በመጀመሪያው ወር ለቤተሰቦች ለሚሰጡ አገልግሎቶች የልዩ ትምህርት ገንዘብ ድጋፍ ማግኘታቸውን በማረጋገጥ ያግዙ።



**የቅድመ ድጋፍ ኤጀንሲዎች ቤተሰብ ከመመዝገቡ እና ኤጀንሲው ለልዩ ትምህርት ገንዘብ ከመከፈላቸው በፊት ብዙ እርምጃዎችን ማጠናቀቅ አለባቸው። አቅራቢዎች የቤተሰብ መረጃን ለመሰብሰብ፣ የልጁን እድገት እና ብቁነት ለመገምገም፣ ሪፖርት ለመጻፍ እና አገልግሎቶችን ለማቀድ ከተንከባካቢዎች ጋር ለመገናኘት ይሰራሉ። ከዚህ ሁሉ ስራ በኋላ፤ አገልግሎቶች ከልጆች እና ቤተሰቦች ይጀምራሉ፤ ሆኖም ግን፣ ኤጀንሲዎች አሁንም ለተጨማሪ አንድ ወር ለልዩ ትምህርት ገንዘብ መክፈል አይችሉም!**

የቅድመ ድጋፍ ኤጀንሲዎች ቤተሰብ ከመመዝገቡ እና ኤጀንሲው ለልዩ ትምህርት ገንዘብ ከመከፈላቸው በፊት ብዙ እርምጃዎችን ማጠናቀቅ አለባቸው። አቅራቢዎች የቤተሰብ መረጃን ለመሰብሰብ፣ የልጁን እድገት እና ብቁነት ለመገምገም፣ ሪፖርት ለመጻፍ እና አገልግሎቶችን ለማቀድ ከተንከባካቢዎች ጋር ለመገናኘት ይሰራሉ። ከዚህ ሁሉ ስራ በኋላ፤




ትንሽ የደንብ ለውጥ ለESIT ኤጀንሲዎች ለመጀመሪያው ወር ብቁ ለሆኑ ህጻናት ለልዩ ትምህርት ገንዘብ እንዲከፍሉ በመፍቀድ የገንዘብ ድጋፍን ይጨምራል። ይህንን ለውጥ ማድረግ የሚችለው የህግ አውጭው ብቻ ነው::

# ቅድሚያ 3

## የሥራ ቅጥር እና የማህበረሰብ አካታች የሆኑ አገልግሎት አቅራቢዎች የሚከፈሉትን መጠንን በመጨመር፤ I/DD ያላቸው ሰዎች ሥራ እንዲያገኙ እና እንዲቀጥሉ፣ እና በማህበረሰቦቻቸው ውስጥ እንዲታቀፉ በማድረግ ያግዛል።


የቅጥር እና የማህበረሰብ ማካተት አገልግሎቶች፣ I/DD ያላቸው ግለሰቦች ስራ እንዲያገኙ እና እንዲቀጥሉ እንዲሁም ማህበረሰባቸውን እንዲያገኙ ያግዛቸዋል። ሥራ ያላቸው ሰዎች በገንዘብ የተረጋጉ፣ የበለጠ ራሳቸውን የቻሉ እና ለሠራተኛ ኃይል እና ኢኮኖሚ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ይህም ሁሉንም ይረዳል። ሥራ ያላቸው እና ማህበረሰባቸውን ማግኘት የሚችሉ ሰዎች አዳዲስ ጓደኞችን በማፍራት እና አዳዲስ ክህሎቶችን በመማር ይጠቀማሉ።

ሰዎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ሥራ እንዲያገኙ እና እንዲቀጥሉ የሚያግዙ የቅጥር እና የማህበረሰብ አካታች አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ክፍት የስራ መደቦችን መሙላት አይችሉም። የማህበራዊ እና የጤና አገልግሎቶች DDA ለህግ አውጭው አገልግሎት አቅራቢዎች የስራ መደቦችን ለመሙላት እና ለአገልግሎቶች ወጪዎችን ለመሸፈን ምን ያህል የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ የሚያብራራ ጥናት በ2022 ሰተዋል። ህግ አውጭው በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን ቢያቀርብ፣ 81% የሚሆኑት የኪንግ ካውንቲ አቅራቢዎች አሁን ያሉትን ሁሉንም ተሳታፊዎቻቸውን ሙሉ በሙሉ ማገልገል እንደሚችሉ፣ 86% የሚሆኑት ደግሞ ሥራ የሚፈልጉ አዳዲስ ተሳታፊዎችን መቀበል እንደሚችሉ ይናገራሉ።


**እያንዳንዱ ለሥራ ቅጥር ድጋፍ የሚውል ዶላር፣ ወደ ኢኮኖሚው 60 ሳንቲም ከመመለስ ጋር እኩል ነው።**

**በቅርብ ጊዜ በተደረገው የአቅራቢዎች ዳሰሳ ላይ በመመስረት፣ ተመኖች ወደ ሚመከሩት ደረጃዎች ቢያድጉ፣ ብዙ አቅራቢዎች አሁን ያሉ ተሳታፊዎችን ሙሉ በሙሉ ለማገልገል እና ለስራ ፍላጎት ያላቸው አዳዲስ ተሳታፊዎችን መውሰድ ይችላሉ።**

አሁን ያሉ ተሳታፊዎችን ሙሉ በሙሉ ማገልገል




አዲስ የሚደገፉ የሥራ ቅጥር ተሳታፊዎችን ይውሰዱ .




በቅርቡ በተደረገ ጥናት መሰረት፣ ከአቅራቢዎች መካከል 43% ብቻ የሚሆኑት አሁን ያለው ተመን ተሳታፊዎችን ሙሉ በሙሉ ለማገልገል እንዳስቻላቸው አጋርተዋል።




# ቅድሚያ 4

## አቅምን ያገናዘበ መኖሪያ ቤት እና የመኖሪያ ቤት ድጋፎች I/DD ላለባቸው ሰዎች መኖራቸውን በማረጋገጥ ያግዙ።

በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ፣ ወደ 37,000 የሚጠጉ የአእምሯዊ እና የእድገት እክል ያለባቸው (I/DD) ጎልማሶች የመኖሪያ ቤት ዋስትና ችግር እያጋጠማቸው ነው።

I/DD ያላቸው ሰዎች ከድጋፍ አገልግሎቶች ጋር አቅምን ያገናዘበ መኖሪያ ቤት ያስፈልጋቸዋል።

ያልተሟሉ የመኖሪያ ቤት ፍላጎቶችን ለመሙላት **37,000** ተጨማሪ ክፍሎች ያስፈልጋሉ።



መታወቂያ ላላቸው የ **IDD** ግለሰቦች የተፈጠሩ **1,328** የ **HTF** ክፍሎች

**IDD** ላለባቸው ግለሰቦች ያለው የመኖሪያ ቤት ከጠቅላላው ፍላጎት ከ**4%** ያነሰ ያሟላል።
የተገመተው ያልተሟላ የመኖሪያ ቤት ፍላጎት በHTF IDD የተቀመጡ ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር፣ ግዛት አቀፍ ፖርትፎሊዮ



ከ**10 (11%)** አንዱ **(1)** በኪንግ ካውንቲ የቤት እጦት ያጋጠማቸው ሰዎች **IDD** እንዳላቸው ሪፖርት አድረገዋል።

የቤቶች ትረስት ፈንድ (HTF) በኪንግ ካውንቲ ውስጥ በተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው የመኖሪያ ቤት ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ ጠቃሚ ምንጭ ነው። ቋሚ የገንዘብ ድጋፍ ምንጮች ለHTF እና ለሌሎች የግዛት እና የአካባቢ ቤቶች አማራጮች ያስፈልጋሉ። ቋሚ የገንዘብ ምንጮችን በመፍጠር እና ተጨማሪ ገንዘብን ወደ HTF በመጨመር፣ ግዛቱ ተደራሽነት ያላቸውን እና ተመጣጣኝ ቤቶችን ማሳደግ ይችላል። የአካባቢ መኖሪያ ቤቶች የገንዘብ አማራጮችም ያስፈልጋሉ። ይህም፣ ጥገና እና የኦፕሬሽን የገንዘብ ድጋፎችን ለትርፍ ያልተቋቋሙ የመኖሪያ ቤት የቤቶች አቅራቢዎችን የረጅም ጊዜ ባለቤትነትን ማድረግን ይጨምራል።

የመኖሪያ ቤትን በተመለከተ፣ I/DD ላለባቸው ግለሰቦች ተደራሽነት ቁልፍ ነው። ከተደራሽ ቤቶች ውስጥ አንዱ በማህበረሰብ የመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሰው ኃይል የሚሰጠው ድጋፍ ነው። ይህ የሰው ሃይል በተከታታይ በቂ የገንዘብ ድጋፍ አልተደረገለትም። በማህበረሰብ የመኖሪያ አገልግሎት ማህበር መሠረት፣ ወደ 50% የሚጠጉ ልምድ ያላቸው የሰው ኃይል በየዓመቱ ይለቃል። የአቅራቢዎች የዋጋ መጨመር በዚህ ረገድ ያግዛል። በDSHS DDA ተጨማሪ የመኖሪያ ቤት ድጋፍ አገልግሎት ሠራተኞችን መደገፍ፣ በቤቶች እና በድጋፍ አገልግሎቶች መካከል ያለውን ቅንጅት ለማሻሻል ይረዳል።

ማኅበረሰባችን የመኖሪያ ቤቶችን ማፈላለግ አስቸጋሪ እንደሆነ ይነገራሉ። ይህም በተለይም ለBIPOC ቤተሰቦች ከእንግሊዝኛ ሌላ የቤት ቋንቋ ላላቸው እውነት ነው።



## ቅድሚያ 5

I/DD ያላቸውን ሰዎች በብቃት ለማገልገል እንዲረዳ፣ ተጨማሪ በችሎታ የባህሪ ጤና አቅራቢዎችን ይቀጥራል፤ ያሰለጥናል።




ብዙዎች የባህሪ ጤና አቅራቢዎች I/DD እና የባህርይ ጤና ፍላጎቶች ያላቸውን ሰዎች በማገልገል ረገድ ልዩ ስልጠና እና ልምድ ያንሳቸዋል። ልዩ ሥልጠና የባህሪ ጤና አቅራቢውን በትክክል እንዲመረምር እና ሰዎችን የሚሰማቸውን ምልክቶች በመረዳት እንዲደግፍ ይረዳል፣ ይህም I/DD ላለባቸው ሰዎች የተለየ ሊመስል ይችላል። ልዩ ሥልጠና በችግር ጊዜ I/DD ያለባቸውን እና ወደ ድንገተኛ ክፍል ውስጥ ለማረጋጊያ አገልግሎት የሚመጡትን ሰዎችን ቁጥር ለመቀነስ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።



## የማህበረሰብ ድምፅ

ማኅበረሰባችን የመኖሪያ ቤቶችን ማፈላለግ አስቸጋሪ እንደሆነ ይነገራሉ። ይህም በተለይም ለBIPOC ቤተሰቦች ከእንግሊዝኛ ሌላ የቤት ቋንቋ ላላቸው እውነት ነው።

ልዩ ስልጠና የባህሪ ጤና ቴራፒስቶችን ቁጥር መጨመር በአንዱ መንገድ፣ በI/DD ውስጥ ልዩ ለሆኑ የተማሪ ብድር ክፍያ እና የይቅርታ ፕሮግራሞችን መደገፍ ነው። በሌላ መንገድ የቴራፒስቶችን ቁጥር ለመጨመር፣ አሁን ያሉ አቅራቢዎችን የI/DD እና ባህሪ የጤና ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች እንዴት ማወቅ እና ማከም እንደሚችሉ በተመለከተ ማሰልጠን ነው።



በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ ከ**5 (37%)** ውስጥ ወደ **2** የሚጠጉት ለ **DDA** አገልግሎቶች ብቁ የሆኑ ሰዎች የባህሪ ጤና ህክምና ፍላጎቶች አሏቸው።

የማህበረሰቡ አባላትበኪንግ ካውንቲ የተስተናገደ የማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ላይ፣ I/DD ላለባቸው ሰዎች የባህሪ ጤና አገልግሎት ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆኑ እና ብዙ ጊዜ ቋንቋቸውን በሚናገሩ እና ባህላቸውን በሚጋሩ ሰዎች እንደማይሰጡ ሪፖርት አድርገዋል።